PANORAMA # XLI

## የትዝብት አድማስ

መስከረም 2 ቀን 2001 ዓም

## እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሳችሁ !

በተለመደው ባኅልና ዕምነት ከሆነ ዘመነ ማቴዎስ የሰላም ዓመት ነው ይባላል። ይኸ አዲስ የገባው ዘመንም፥ ዘመነ ማቴዎስ ስለሆነ በሀገራችን ሰላም ይወርዳል ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ጥቂቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ከአለፉት ሠላሳ ስድስት ዓመታት ወዲህ በየአራት ዓመታት የተለወጡትን የአራት ወንጌላውያን ስም ብናሰላው እንኳ፥ ዘመነ ማቴዎስ 9 ጊዜ እየመጣ እንደሄደ እንገነዘባለን። በባህል አኳያ ሲታይ፥ ያው እንደ ተለመደው፥ የዘ ድሮው ዘመነ- ማቴዎስ እንደዚሁ፥ የተለየ ነገር ለሀገራችን ሊያመጣ እንደሚችል ብዙ አማኝ ተስፋ በማድረጉ፥ ተስፋህ ወደ ዕውነት ይለወጥልህ ማለቱ የሚከፋ አይሆንም። በሰላሳ ስድስት ዓመታት ውስጥ፥ ዘመነ ማቴዎስ ዘጠኝ ጊዜ እንደተለዋወጠ ሁሉ፤ ሦስት የሥርዓት ለውጦችም መከናወናቸው የታወቀ ነው። ሦስት አምባገነኖችን የቀያየረው የሀገራችን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ግን ምንም ያሳየው የረባ ለውጥ እንደሌለ፥ የአሁኑ ሁኔታችን ግልፅ አድርጎ አሳይቶናል። ጉልቻዎቹ ተለወጡ እንጅ የሀገራችን ሁለንተናዊ ሁኔታ ያው ነው። ዋርካው አፍርቶ አዕዋፍን ካልመገበ፥ ዝ ም ዘንቦ፥ እህል ካላበቀለ፥ አዝመራው ደርሶ ሕዝብ ካላጠገበ፥ ዘመን ተለውጦ አዲስ ህይወት ካላስገኘ፥ ሥርዓትም ተለውጦ የተሻለ ኑሮ ካላጎናፀፈ፥ "ጉልቻዎቹ ቢቀያየሩ ወጡን አያጣፍጡትም" የተባለው ሁኔታ ነው እውን የሚሆነው። ለእኛም "ሺ ቢታለብ ያው በገሌ" እንዳለችው ድመት መሆን ነው ።

በዴሞክራሲ የሚተዳደሩና በዘመናዊ ሥልጣኔ የተራመዱ ሀገራት መሪዎች በየዓመቱ ዘመን ሲለወጥ ለአዲሱ ዓመት የሚሆን የሥራ እቅዳቸውንና የልማት ፕሮግራማቻውን፥ አዘጋጅተው፥ ለሚመሩት ሕዝብ ይፋ ያደርጋሉ። ስለአለፈው ዓመት የሥራ ውጤታቸው ዘገባ ያቀርባሉ። ሳይሰራ ስለቀረው ደግሞ ለምን እንዳልተፈፀመ በአሳማኝ ምክንያት የተደገፈ ዘገባ ያቀርባሉ። ገለፃ ይሰጣሉ። የሀገሬው ዜጋ የሚሳተፍበት አዲስ የሥራ መስክ ይከፍታሉ። ግልጽነትና ተጠያቂነት የአስተዳደራቸው ዓብነት በመሆኑ፤ ከሕዝብ የሚደበቅ አንዳችም ጉዳይ አይኖርም። የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት አንዱ ከሌላው ጋር በሕግ የተጣመረና የተደጋገፈ በመሆኑ፥ እንዲሁም የመንግሥቱ አካላት አወቃቀራቸው፥ ልኬታቸው ተጠብቆ፥ አንደኛው ከሌላኛው ጋር የሥልጣንና የተግባር ኃላፊነታቸውንና ወሰናቸውን አውቀው ሕዝብ ያገለግላሉ። አንደኛው የሌላኛውን ወሰን አያልፍም። ሕገ መንግሥቱ ከደነገገለት የሥልጣን እርከን አይዘልም። ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ የሕግ የበላይነት ይከበራል ብሎ መደምደም ይችላል።

በአዲሱ ዓመትም አዳዲስ የልማት ዕቅዳቸውን፥ የዕድገት አውታራቸውን፥ የሥራ መርኃ-ግብራቸውን ለሕዝብ ያቀርበሉ፥ በፓርለማ ያፀድቃሉ፥:: አዳዲስ የሥራ መስክ ይከፍታሉ:: በአለፈው ዓመት የተከናወኑትን የሥራ ውጤት በመመርኮዝ፥ በሰሩት ሥራ ሲወደሱ፥ ባልሰሩት ሥራ ሲወቀሱ፥ ሁሉንም በፀጋ ይቀበላሉ:: የዲሞክራሲ መሠረቱ አሰራሩና ሂደቱ፥ አፈፃፀሙና ዉጤቱ በዚህ ዓይነት ይካሄዳል:: የሚሻሻል፥ የሚሰተካከል፥ የሚሰረዝ የሚለወጥ ካለ፥ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው ደንብና ሥነሥርዓት መሠረት ይፈፀማል:: እንደ ሕዝቡ ፍላጎትና ፈቃድ እንጅ፥ እንደ መሪዎች መኖትና ጥቅም የሚሆን ነገር አይኖርም:: በባኅላዊ እሴቶች ላይ ትኩረት የሚሰጡ መንግሥታትም በአዲስ ዓመት፥ እስረኞችን መማርና መፍታትም የተለመደ ነው:: በመሠረቱ፥ የወህኒ ቤት ተቋማት ዓላማና ፍልስፍና ጥፋተኞችን ለማረምና ለመመክር ስለሆነ፥ የአማክሮ ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ምህረት ቢያገኙ የህገራችን የቆየ አስመሰጋኝ በኅላችን እንጅ፥ አምባገነኖች እንደሚያደርጉት ለበቀልና ለቆጭት መውጫ አልነበረም::

ወደ ዛሪይቱ ሀገራችን ሁኔታ ስናተኩር ግን ሀቁ የተለየ ነው:: በሀገራችን በሥልጣን ላይ የሰፈሩት ጉዶች፥ ከዴሞክራሲው ሥርዓትም ሆነ ከሀገር ባሕል የተጣሉ ጭራቆች ናቸው:: የዘመን መፈራረቅ፥ የአዲስ ዓመት መምጣት-መሄድ፥ የመሪዎች መለዋወጥ፥ የሥርዓት መፈራረቅ፥ እንደተለምዶ ክስተት ከመታየት ካለሆነ በስተቀር፥ትርጉም ያለው ለውጥ አያመጣም:: የሚመጣው መሪ፥ ሀገር አጥፍቶ፥ ሕዝብ ጨቁኖና አደህይቶ፥ ራሱንም አበልፅጎ ሲሰለቸው ሀገር አጥፍቶ ሲጠፋ፥ በእርሱ እግር የሚተካው ደግሞ በአዲስ ጥርስ፥ ልክ እንደሄደው የራሱን ድርሻ ይቦጭቃል፤ያደማል:: ልዩነቱ ፥ አዲስ የተተካው የሄደውን በሚያስመሰግን መልኩ፥ ሀገር የማጥፋቱን ድርጊት ማከናወኑ ብቻ ነው:: አጥፊ መንግሥታት ሀገር አጥፍተው ሲጠፉ፥ አለቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን መሠረቱን ሳያናጋ፥ ታሪኩን ሳያፋልስ፥ አንድነቱን ሳይጎዳ ፥ ዘመንና ታሪክን እየታዘበ፥ መከራና ፍዳውን እንደተሸከመ ህይወቱን ይገፋል:: በኢትዮጵያ የዘመናት መለዋወጥና የመሪዎች መፈራረቅ፥ የሕዝቡን መከራና ፍዳ፥ ረሀብና በሽታ፥ ድህነትና ጭቆና አያቃልሉትም፥ አይለውጡትም:: እያባባሱት ከመሄዳቸው በስተቀር:: ለእኛ፥ ማርቆስ፥ በዮሀንስ፥ ሉቃስ፥ በማቲዎስ ቢተኩ፥ ቢለዋወጡ፥ ያመጡልን፥ የሚያመጣልን ለውጥ የለም:: እስካሁን! የዘመናት መፈራረቅ የተፈጥሮ ህግ በመሆኑ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የሚመጣውን በተስፋ ከመቀበል፥ የሚሄደውንም በትዝብት ከመሸኘት በስተቀር፥ ሌላ ምርጫን በራሱ ትግል አላስመዘገበም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ፥አዲስ የሚመጣን አምባገነን በአርምሞ የሚቀበለው፥ ምናልባት ዘርፎ ከሄደው አምባገነን የተሻለ ነገር ይገኛል ከሚል ቀቢፀ-ተስፋ ነበር:: ግን አልሆነም አይሆንምም:: ይህ ዓይነቱ ክስተት ደግሞ ዘመናት በተፈራረቁ መጠን ይቀጥላሉ እንጅ የሚቆሙበት ሁኔታ አልታየም:: እስከዛሬ! ዘመናቱ ሲመጡና ሲሄዱ፥ የሕዝባችን መከራና ስቃይ፥ ረሀብና በሽታ፥ ድህነትና ጉስቁልና፥ ጭቆና፥ ስደትና እስራት እስካሁን በከፋ መልካቸው ቀጥለዋል:: አዲሶቹ አምባገነኖች ሲመጡ የተረከቡትን ከማማባባስ በስተቀር፥

*ምንም የተሻለ ለማምጣት አይሞክሩም:: አይፈልጉምም:: ሲጠፉ ደግሞ ÷ የባሰውን ጥለውብን ከመሄድ በስተቀር ለትዝብትና ለስንቅ ያህል እንኳን ትንሽም ቢሆን ችግራችንን ይዘውልን አይሄዱም:: የሰላም ማጣትና የጦርነት አባዜ÷ ረሀብና ስደት÷ በሽታና ድኅነት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አንድ አምሳል አንድ አካል በመሆናቸው የብሄራዊ መለያችን መስለው መወሰድ ከጀመሩ ዓመታት አልፈዋል:: ዘለዓለም ዋይታ! ዝ ተ -ዓለም ሰቆቃ በቀር የተሻለ አይመጣም:: ወያኔዎቹ እስካሉ ድረስ ደግሞ ሰላም ወርዶ መረጋጋት ሰፍኖ÷ ወደ ልማትና ዕደገት ጎዳና እናመራለን ማለት ዘበት እየሆነ መሄዱ የተለመደ ክስተት ሆኗል:: ታላቁ መጽሐፍም÷ <u>ሰላም ሰላም ይላሉ እንጅ÷ ሰላምን አያገኙም</u>÷ ያለውም ይህንን የኛውን ዓይነት ሁኔታ ለመግለፅ እንደሆነ ይታመናል:: ዘመን በተለወጠ ቁጥር÷ አዛውንት ሲመርቁ÷ " ያለፈውን መከራ የሚመጣውን ደስታ ያድርግልን" ይላሉ:: ስለመጭው አዲስ ዓመት ያላቸውን በጎ ራዕይና ተስፋ ለመግለፅ ሲሉ ነበር:: ተጨባጩ የሀገራችን ሁኔታ ግን÷ የተገላቢጦሹን ነው የሚናገረው:: ያለፈውን እንደ ደስታ የሚያስቆጥር የሚመጣው ደግሞ÷ የባሰ መከራ አዝሎ የሚመጣ እየሆነብን ነው የምንቸገረው:: ብሩኅ ተስፋ የሌለው ሀገር÷ የሕዝብን ሰቆቃ የማያስወግድ ሥርዓት÷ ከችግርና ከበሽታ አዙሪት የማያወጣ መንግሥት የሚቀያየርባት ኢትዮጵያ! ለዚህም ይመስለናል÷ ሕዝባችን÷*

> *ምነው አምና በሞትኩ እንዲያ እንዳማረብኝ÷*
> *የዘረኛ መንግሥት ሳይጫወትብኝ÷*
> *የሀገሬንም ጥፋት አምላክ ሳያሳየኝ::*

*እያለ የኢትዮጵያ ሕዝብ÷ ዘመን በተለወጠ ቁጥር የሚያንጎራጉረው:: አዲስ ዓመት የአዲስና የብሩኅ ተስፋ ፍንጣቂ ካላመጣ÷ የሰቆቃው እንጉርጉሮ የሚያቆም አይሆንም::*

*የኢትዮጵያ አረመኔ ገዢዎች ዘመን ሲለወጥ÷ ለአዲሱ ዓመት የሚሆን የሥራ ዕቅድና የልማት ፕሮግራም ለመዘርጋት የሚያስችል ፕላን ስለማይኖራቸው÷ ሁል ጊዜ በየዓመቱ የባዶ ተስፋ ፕሮፓጋንዳና ዲስኩራቸውን በመምታት ሕዝብ ያደነዝዛሉ:: ትርኪ-ምርኪ ንግግር እያደረጉ ሕዝብን ይሸነግላሉ:: ባለፈው ዓመት እዚህ ግባ የሚባል ሥራ ስለ አልሰሩ÷ ከሰው ፊት የሚቀርብ የሥራ ዘገባ ሊያቀርቡ አይችሉም:: ምናለባት ያከናወኑት ተግባር ካላቸው÷ በአለፈው ዓመት ምን ያህል እስር ቤት እንደገነቡ÷ ስንት አዳዲስ ሰላዮች እንዳሰለጠኑና እንዳሰማሩ ነው ሕዝቡ የሚገነዘበው::÷እስረኛ ሊፈቱ ቀርቶ ስንቱን የጎሊና እስረኞች ወኅኒ እንዳወረዱ÷ ስፍር ቁጥር የሌለው ዜጋ ከሀገር እንዳሰደዱ÷ ምን ያህል ሕዝብ እንደጨፈጨፉና ምን ያህልስ መጠን ያለው የሕዝብ ሀብት እንዳሸሹ ብቻ ነው ማረጋገጥ የሚፈልጉት:: ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ጥፋት እንጅ÷ የልማት ውጤት እንዳልሆነ ጤናማ ጭንቅላት ያለው ዜጋ ሁሉ የሚገነዘበው ነው:: ማነኛው ሀገር÷ በባዶ ፕሮፓጋንዳና በውጭ ምፅዋት የትም እንደማይደርስ÷ የኢትዮጵያ ጨቋኝ ገዢዎች ይወቁት አይወቁት ሌላ ጉዳይ ነው:: የሕዝቡን የማሰብ ኅሊና ግን ዝቅ አድርገው*

ሊገምቱት ከቶ አይችሉም፤ አይገባቸውምም:: ይህ መለስ ዜናዊ የተባለው ግለሰብ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የመጥላትና የማዋረድ አባዜ የተጠናወተው ስለሆነ፥ ይህን ሀቅ ይቀበለዋል ተብሎ አይጠበቅም:: በወታደር ኃይል ሆነ ፤ በስለላ ድርጅት ጥንካሬ ወይም በሰላዮች ስልጠናና ስምሪት ቢሆን ኖሮ፥ በሦስተኛ ዓለም ሀገሮች በሚባልላቸው ሕዝቦች መካከል፥ የኢራኑን ሻህ ባህላቢን የሚወዳደር አልነበረም:: የማታ ማታ የኢራን ሕዝብ ቁጣ ሞልቶ ሲገነፍል ግን፥ ያ ግዙፍ ሰራዊቱ ሆነ፥ አሰፈሪ የነበረው ሳቫክ የሚባለው የስለላ ድርጅቱ ሻሁን ከመውደቅ አላስጠለውም:: ይኽንን የታሪክ ሀቅ ተረድተው ቢሆን ኖሮ፥ የኢትዮጵያንም ሕዝብ ቁጣ የሚያቆመው እንደሌለ፥ መለስና ግብረ-አበሮቹ ማወቅ ነበረባቸው:: ግን ዐይናቸው በዘረኝነት ሞራ ተጋርዷል:: የድንቁርና ዕብሪታቸው የማሰብ ችሎታቸውን አፍኖታል:: ስለዚህ ከውድቀታቸው ከቶም የሚያመልጡ አይደሉም:: ልብ ያለው ልብ ይበል!

የዘመን መፈራረቅ ብቻውን ሰላምን አያስገኝም:: ዘመን ስለተለወጠ ብቻ ሰላም ይገኛል ብሎ እራሱን የሚያታልል ካለ፥ አመለካከቱን እንደገና ማስተካከል ይኖርበታል:: ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት አስቀድሞ መሠረቶቹን መጣል ያስፈልጋል:: የፍትኅ-ርትዕ መከበር፥ የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን፥ የዜጎች እኩልነት መረጋገጥ፥ የሕዝብ ሉዓላዊነት መንገሥ፥ የህግ የበላይነት መገኘት፥ የሰላም መምጣት መሠረትና ምሰሶ፥ ማገርና ግድግዳ ናቸው:: እነርሱ ከሌሉ ሰላም አይኖርም:: ሰላም ከሌለ መረጋገት አይመጣም:: ይህ በሌለበት ደግሞ ወደ ልማት ማተኮር ያስቸግራል:: ልማት ካልተጀመረ ደግሞ ፥ ከድኅነት መውጣት የሚታሰብ ሊሆን አይችልም:: አምባገነኖች ደግሞ ይህንን ሀቅ መቀበል ቀርቶ፥ መስማት እንኳ የሚፈልጉ አይደሉም:: መርኃ ግብራቸው የተቀየሰው፥ እየጮቆኑ፥ እያደኸዩና እያጨፈጨፉ መግዛት በመሆኑ፥ስለ ሰላም መሠረቶች ጉዳይ እንዲነሳባቸው አይፈልጉም:: ሰላምን ለማምጣት ሰላም ነሽዎችን ማስወገድ ደግሞ የሚገባ ነው:: ወያኔ እያለ ደግሞ ሰላም አይገኝም:: ሰላም ነሽዎችን አስወግዶ ዘላቂ ሰላምን ማስገኘት የሚሹ ሁሉ ተቀዳሚ ተግባራቸው የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ማስወገድ ሊሆን የግድ ይላል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ፥እንዲያው በባዶ ሜዳ፥ ሰላም ሰላም ቢሉት፥ ሰላም አትገኝም:: ይኸ የተቀበልነው አዲስ ዓመት ዘመነ-ማቲዎስ ነው:: ታዲያ ዘመነ-ማቲዎስ የሰላም ዘመን ነው የሚል ስያሜ ከተሰጠው፥ ሰላምን ለማግኘት፥ ሁሉም ዜጋ፤ ቋሚ ሠላምን ሊያመጣ የሚያስችል ሁለ ገብ ትግል ለማድረግ ቆርጦ መነሳት አለበት:: በዕርግጥም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ለጭቆና አለመመቸቱን እያረጋገጠ ሕዝባዊ አመፅ ከማካሄድ ሌላ አማራጭ አይኖረውም:: በዘመነ ማቴዎስ ፤ የሕዝብ ትግል ውጤት እያስመዘገበ ነው ማለት መቻል አለብን:: የነፃነት ምዝገባ ለነገ የሚተላለፍ፥ ወይም ለተከታዩ ትውልድ የሚወረስ ሊሆን አይገባውም:: እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ድርሻ እየተወጣ፥ ግዴታውን እያሟላ ካለፈ፥በታሪክና በመጭው ትውልድ የመሰገናል እንጅ ሊወቀስ አይችልም::

እኛ በበኩላችን በአዲሱ ዓመት አዳዲስ የትግል ስልቶችን እየቀየስን ትግላችንን ከመቀጥል በቀር ሌላ ብሔራዊ አጀንዳ የለንም:: ይህንን ዘመን የማይሽረውን

**የትግል ቃል-ኪዳናችንን እያረጋገጥን፥ ለምንታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአዲሱ ዓመት መልካሙን ሁሉ እንመኛለን፡፡ እንኳ ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ!!!**